# ተጠያቂነትን ገንብተን ድርጅት አፍራሾችን እናጋልጥ!

ከአቶ ሰውየው

አምናም ካችአምናም ከዚያ በፊትም እንዳየነው፤ በየድርጅቶች ውስጥ አንዳንድ መሪዎች ነን ባዮች የሚቆሰቁሱትና ገንኖ የሚታየው የእርስ በእርስ መናቆር ዛሬም በሠፊው ዓይኑን ባፈጠጠ የክህደትና የውሸት ውኻርንብር ታጅቦ በእንቶ ፈንቶ መዳማቱ እንደቀጠለ ነው። ስለሆነም ግርግር ለሌባ ያመቸዋል ነውና ትግሉን እንመራለን የሚሉን የተለያዩ ቡድኖችና መሪዎች በየጊዜው በሚፈጥሩት ኹከት ተጠምደን፣ ትኩረት ልናደርግበት የሚገባውን ዋናውን የሀገራችንን ጉዳይ ወደ ጎን በመተዋችን እነሆ ወያኔ በሕዝባችን እያላገጠ ይገኛል።

በተቀዋሚ ድርጅቶች በተለይም የአንድነት ኃይሎች ናቸው ብለን ከፍተኛ ግምት በምንሰጣቸው ውስጥ በተደጋጋሚ አምባጓሮ የሚነሳው ለምንድር ነው ብሎ መጠየቅ በእኔ ግምት የሰውን ልጅ ካንሠር ለምን ይይዘዋል እንደማለት ነው። የካንሠርን በሽታ ተቋቁመው በሙሉ ጤንነት ኑሮአቸውን የሚገፉ ሰዎች ለዚያ ያበቀቻውን የመረመረ ብዙውን ጊዜ በሽታቸው ሳይስፋፋ በጊዜ የመታወቁና አስፈላጊውን ህክምና የማግኘታቸው ለመሆኑ ሁላችንም የምንስማማበት ነው። እኛም ድርጅት ማለት በርከትከት ያሉ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ሰዎች አብረው ለአንድ ዓላማ በአንድ ወቅት የሚሰባሰቡበት እንደመሆኑ መጠን በየአቅጣጫው መሳሳብ ያለ መሆኑን መገንዘብና በየድርጅት አመራር ውስጥም አፍራሽነት በማንኛውም ጊዜና ቦታ በማንኛውም ግለሠብ ሊከሰት እንደሚችል አምኖ መቀበል፣ ተዘጋጅቶም መገኘት ያሻናል። ቁም ነገሩ ግን መሳሳቡ የሚፈጥራቸውን ቅራኔዎች የድርጅቱን ዓላማ በማያቃውስና የውስጠ ደንቡን በማይጥስ ዘዴ ባግባቡ በጊዜ የመፍታት ችሎታ የመኖር ያለመኖር ጥያቄ ነው። ዕውነተኛ መሪዎች የሚፈተኑንም ይሄኔ ነው።

ይህን ጽሑፍ እንዳቀርብ ያነሳሳኝ በቅርቡ ወደ መድረክ ብቅ ካለ ጥቂት ጊዜ ያለው የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ውስጥ የተነሳውን ግርግር ፈር ለማስያዝ የድርጅቱ አመራር አባላት በአከታታይ በመሰብሰብ በረጋታ ለመቋጨት ያደረጉትን ጥረትና ያሳለፉትን ውሳኔ በማድነቅ ለመደገፍ፤ ያሳለፉትንም ውሳኔ ካነበብኩ በኋላ የድርጅቱን ሕግ በመጣስና በማን አለብኝነት የድርጅቱ አመራር አባልና ቃል አቀባይ ሆና ትሠራ የነበረችው ዶ/ር አበባ ፈቀደ የተረከበችውን ኃላፊነት ወደ ጎን በመተው ከሁለት ወራት በፊት ለብቻዋ በድርጅቱ ስም በከፈተችው መድረክ ላይ እየተካሄደ ያለውን የውሸት ጋጋታና ሀቀኛ መሪዎችን የማጣጣል ዘመቻ ለመቃወምና ለማውገዝም ጭምር ነው። በተለይም እንደ መግለጫው አገላለጽና እኔም ከተረዳሁት አንፃር የድርጅቱ ንብረት የሆነው የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ራዲዮ ጣቢያና ድረ-ገጽ በቁጥጥሯ ውስጥ እንዳለና ብዙሃኑ ከሚፈልጉት ዓላማ ውጭ የሌላ ዓላማ ተላጣፊ ማድረግ ተጠያቂነትን ሊያመጣ እንደሚችል እንድትረዳልኝ ለማስገንዘብ ነው። ከብዙሃኑ ዕምነትና ስምምነት ውጭ የድርጅት ንብረት መውሰድ በኔ ዕምነት ይቅርታ ይደረግልኝና እህቴ ዶ/ር ብትሆንም የሚያስተዛዝብና የሚያስፈርጅ ነው። በዓለም አቀፍ ተበትነው ያሉ እህቶቻችንና እናቶቻችን ለሚደርስባቸው ሰቆቃ ድምጽ ሊሆን ይችላል ብለን ብዙዎቻችን ትልቅ ግምት የሰጠነውን ድርጅት ገና ከጅምሩ የማያስፈልግ ውጥረትና መነታረክ በማንሳት ብሎም አመራሩ ተሰብስቦ በአብዛኛው ድምፅ የተደገፈ ምፍትሄ ሲቀርብ ዶ/ር አበባ የብዙሃኑን ውሳኔ በመጣስ የድርጅት ስምና ንብረት ይዛ መንጎዷ ከእርሷ የማልጠብቀው እንዲያም ሲል

የሚያሳዝን ጸረ-ዴሞክራሲያዊነት ነው። ማንም መሪ ነኝ ባይ ከብዙኃኑ ድምፅ በልጠና ራሱን ከድርጅት መተዳደሪያው ደንብ በላይ አድርጎ መቅረቡን ምንም ዓይነት ምክንያት ቢደረድር በሕብረተ-ሰባችን ነውር መሆኑን መሪዎች ነን ለሚሉን ሁሉ ሊጥሱት  የሚይገባቸውን መሥመር አሥምረን በማስቀመጥ፤ በማናለብኝነትም ሲተላለፉ ቶሽ ብለን መንገዱን በማሳየትና የድርጅታቸውን ዓላማ እንዳይረሱ ማስገንዘብ የእያንዳንዳችን ግዴታ ነው እላለሁ።

በነገራችን ላይ በወቅቱ ለሁለቱም ወገኖች መድረኮቻቸውን ዘግተው ችግራቸውን በውስጥ እንዲጨርሱ ዶ/ር አበባ በከፈተችው መድረክ ላይም በመውጣት (ምንም እንኳ በጊዜው ዶ/ር አበባ ብታስቆመኝም) ሃሳብ ካቀረቡት ወገኖች አንዱ ነበርኩ። እንዲያውም አንዳንድ ወንዶችና የድርጅቱ አባላት ያልሆኑ ሴቶች ዶ/ር አበባ በከፈተችው መድረክ ላይ ወጥተው በጊዜው በማያገባቸው ችግር ራሳቸውን ጥልቅ አድርገው የችግሩ መንስኤ ገነትና አስቴር ስለሆኑ መባረር አለባቸው ብለው ሲደነፉ በነበረበት ወቅት ማለት ነው።

አንዳንድ ወገኖች በምሰጣቸው አስተያየቶች አይደሰቱም። እንዲያውም አክራሪና ተሳዳቢ በማለት ልዩ ቅብ ሊሰጡኝ የሚዳዳቸውም አሉ። ሰው ያልሆነውን ካለማስረጃ የምወነጅል ቢሆን ሁሉም በተገባኝ። ነገር ግን ባደባባይ በይፋ ሁሉም የሚመሠክረውን ስርቆት ሌብነት ነው ማለቴ ሊያስወቅሰኝ አይገባም። ይልቁንስ ሁሉም በየቤቱና በቅርብ ከሚያምነው ጋር የሚነጋገርበትንና የሚያምንበትን ዕውነታ መናገር ነውር እንዲሆን የሚገፋፉንም (በተዘዋዋሪ መንገድ ሳንሱር በራሳችን ላይ እንድናደርግ ማለት ነው) ማንነታቸው እንዳይጋለጥ የሚሰጉቱ እነዚያው ሞጭላፊዎቹና የድርጅት አፍራሾቹ ስለሆኑ በዝምታችን የሌቦችና የአጭበርባሪዎች ሰለባዎች እንዳንሆን እሰጋለሁ። አዎን ኢትዮጵያውያን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ በዓለም ተበትነን በምንገኝበት ወቅት በርካታ ድረ-ገጾች፣ ራዲዮ ጣቢያዎችና የመሳሰሉት ዘመናዊ የብዙሃን መገናኛዎች እንዳሉን ግልጽ ነው። የነዚህ ተቋማት ባለቤቶቹ ግን በአብዛኛው ተጠያቂነትን ከመገንባት ይልቅ የገንዘብ መሥሪቸው አድርገውና የገደል ማሚቶዎች ሆነው ከነፈሰው ጋር የሚነፍሱ ራሳችንን ገንዘን ካስቀመጥንበት የሬሳ ሳጥን ውጪ አውጥተን ነፃ በሆነ መንገድ ሃሳቦች እንድናሸራሽርና ተጠያቂነትን እንድንዳስስ ሲያረጉ አይታዩም። እንግዲህ ነውሩን ነውር፣ ሌባውን ሌባ፣ አካፋውን አካፋ በማለት የጨዋታውን ሕግ ባለማስከበራችን እነሆ ላለፉት 17 ዓመታት ወያኔ ጠንክሮ ሳይሆን ሕዝቡን እንመራለን በሚሉን ወገኖች እርስ በርሳችን በጎሪጥ እንድንተያይ፤ መተማመን ጠፍቶ ሁሉም እንደፈሳ ዝንጀሮ ለየብቻው ቁጭ እንዲል እኛኑ በኛው በታትነን እንገኛለን። ምክንያት ብትሉኝ በተደጋጋሚ የሚያበጣብጡንን መሪ ተብዬዎች ከሀቀኞቹ መለየትና ተጠያቂ ማድረግ አለመቻላችን ወይም ይሉኝተኞች ሆነን ዝም በማለታችን ነው ባይ ነኝ።

አንድ ዕውነታ ግን አለ። ከትላንት በስቲያ መሳሪያው በጃችሁ ብለው ወገን ካለፍርድ ሲታጨድ ያዳመቁ ፕሮፌሰሮች ትላንት ወያኔን ሊያነግሱ ልጆቻችን ናቸው ብለው ሲመጡ ደፍረን እርስዎማ ምን የሞራል ብቃት ኖሮዎት አለማለታችን፤ እነሆ ዘንድሮ ደግሞ በአሚሪካ ምክር ቤት እድሉን አግኝታ “በእሥር ያንገላታትን” ወያኔ ማንነቱን ማጋለጥ የምትችልበት ሁኔታ እንኳን ሲፈጠርላት በኢትዮጵያ የፖለቲከኛ እሥረኞች ቁጥር መቶ ያለችዋን ፍርደ ገምድል ትምራችሁ ሲሉን በየቤታችን አጉረምርመን ቁጭ ስላልን፤ ወይም ወያኔ ሥልጣን ሲይዝ ያለፉበትን ሁሉ ረግመው እጅ መንሻ ይዘው ሩጠው ሕጋዊነት ቅብ ሲሠሩለት የነበሩ ዶ/ር ተብዬዎች ዛሬ እኛ እንምራችሁ ብለው የውሸት ድርጅት እየቀፈቀፉ ያኔ እነሱ በውስኪ ሲራጩ በእሥር የተንገላቱትንና ዛሬም የሚንገላቱብንን መሪዎች ሲያጣጥሉ ዝም ብለን ተከትለን፤ በኢትዮጵያዊነታቸው ጽኑ የሆኑ ድርጅቶችን ለማፍረስ አንጃኝነትን ፈጥረው መሪዎቻቸውን ባደባባይ በማጣጣል ተሰሚነት እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ፤ ባንጻሩ ግን

ወገኖቻችንን በአማራነታቸው ከገደል ተወርውረው እንዲጣሉ ያደረጉ የኦነግ ወንጀለኞች እንዲወዷቸው "በኢትዮጵያዊነታቸው አይናፋር ሁነው እንጂ በአንድነት ሊያምኑ ይችላሉ" ብለው ገና ኢትዮጵያዊነትን እስኪማሩ እንድንጠብቃቸው ሊያስተምሩን የሚሹ አልጫዎችና ማፈሪያዎችን እንደበግ ባኣ ባኣ ብለን ተግቸልችለን ተከትለን፤ ነገ ዴሞክራሲ ከነሱ መጠበቅ በኔ ዕምነት ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ ነውና ዝምታው ይብቃ ነው መልዕክቴ። ድርጅት የማበጣበጥ የኋላ ታሪክና ልምድ ያላቸው አፍራሾች በየአማራሩ እየተሰገሰጉ የድርጅት ሕግ ጥሰው ስሙን፤ ንብረቱን ይዘው ሲነጉዱ እኛም ተከትለን ሳንጠይቅ አብረን ሆ! ማለት እኛንም በኃላፊነት የሚያስጠይቅ መኖሩን አለመረዳት ትልቁ ጥፋታችንና ድክመታችን ነው። ሃበሻ ጆሮና ልቡና ያለው ይስማ! ተጠያቂነትን በመገንባት ትግላችንን የሚያዳክሙብንን መሪ ተብዬዎችን ማንነታቸውን በማጋለጥ መንጥረን ማውጣት ግዴታችን ነው! ዕውነትን ተናግሮ የመሸበት ማደር ይሿል ይሄው ነው።

እምቢኝ ለዘረኝነት፣ ለበታኞችና፣ ለባንዶች!
ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል!
ሀቀኛ መሪዎቻችንና ድርጅቶቻችንን እንደግፍ!
አስመሳይ መሪ ተብዬዎችንና አፍራሾችን ሳንፈራ እናጋልጥ!

አቶ ሰውየው (ኅዳር 27 2001 — ከሰሜን አሜሪካ)
(December 7, 2008)